# አሲምባ ርዕስ አንቀጽ

Editor’s Note ቁጥር 2/2010

## ሠርገኛ መጣ በርበሬ ቀንጥሱ!

### “የኢትዮጵያ ባለድርሻዎች ጉባኤ የማህበረሰባዊ ድርጅቶች ትብብር”
### በዚህ ሳምንት መጨረሻ ስለጠራው የፖለቲካ ድርጅቶች
### የትብብር ጥሪን አስመልክቶ ልንመረምራቸው የሚገቡን ነገሮች፡-

በመጀመሪያ በኢትዮጵያ ሕዝብ በየአቅጣጫው የተካሄደው የማያቋርጥ ትግልና ዓመጽ ተወጥሮና ተገዶ የወያኔ መንግሥት በዚህ ሳምንት በሀገራችን ታሥረው የነበሩ ጥቂት የፖለቲካ የሕሊና እሥረኞችን መልቀቁ ሀገር ወዳዶችን በሙሉ የሚያስደስት ቢሆንም፤ ከእሥር ከተለቀቁት መካከል አቶ በቀለ ገርባ በአሚሪካው ራዲዮ ድምጽ እንዳሳሰቡን እጅግ በጣም ብዙ የኅሊና እሥረኞች አሁንም በየማጎሪያ ጣቢያዎች ፍዳቸውን እየቆጠሩ እንደሆኑና ሁሉም መፈተታት እንዳለባቸው ነው። ለነገሩማ የወያኔ ሥርዓት የሕዝቡ ትግል አየል ሲልበት ጥቂት የፖለቲካ እሥረኞችን በመፍታት ፋታ የሚያገኝበትን ጊዜ አመቻችቶ ሳይውል ሳያድር ወገኖችን ማሰቃየት መቀጠሉን የወያኔን 27 ዓመታት ጉዞ ለምንረዳ ሁላ ጥቂቶች ተፈቱ ብለን ብዙ ልንዝናና አይጠበቅብንም።

አንዳንዶች ሳያውቁ በየዋህነት፤ የምናውቃቸው ጠማሞቻችን ደግሞ እንደለመዱት የጡት አባቶቻቸው በሚያመለክቷቸው አቅጣጫ ከወያኔ ጋር ዕርቅ በሚል ሽፋን “እንግዲህ ወያኔ እሥረኞችን ከፈታ....የታሠሩትን በሙሉ በመልቀቅ አገራዊ ዕርቅ በማምጣት ኢትዮጵያ ውስጥ አዲስ ምዕራፍ መክፈት ይቻላል። በቂምበቀል የኅሣ ረብሻና ዕልቂት አሸናፊ አይኖርም።” የሚሉ ሰበቦችን በመደርደር፣ የሞቀው የሕዝብ ትግል ላይ በረዶ ሊያፈሱ የሚሯሯጡ እንደሚኖሩ መጠራጠር የለብንም። ደግሞም ብቅ ብቅም እያሉ ነው።  የትግላችን ዓላማ ሥር ነቀል (ወያኔንና የዘር ፖለቲካን ከነ ሰንኮፉ መነጋግሎ ጥሎ በምትኩ ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን የሚተካ) መሆኑን ልንተማመን ይገባናል። የኅሊና እሥረኞችንም አስመልክቶ መታገልም ያለብን ሁሉም የፖለቲካ እሥረኞች ካለምንም ቅድመ ሁናቴ እንዲፈቱ መሆን አለበት። ለምሳሌም ትኩሱ እሬሳ የቀድሞውን አሥረሳ እንዲሉ ወያኔ ወደ አዲስ አባባ ሊገባ ሲልና በሥልጣን ከተደላደለም በኋላ ደብዛቸውን ያጠፋቸው የኢሕአፓ የፖለቲካ እሥረኞች ጉዳይ በአብዛኛዎቹ ፖለቲከኞች፤ “የኢትዮጵያ ሰብአዊ ድርጅት” ነን የሚሉንም ጨምሮ (በሀገር ቤትም ሆነ በውጪ ያሉትን ያካትታል) ሲነገር አይሰማም። ከጥቂት ዓመታት በፊት የቀድሞ ወያኔ የነበረው ገብሩ አሥራት እነ ደብተራው መገደላቸውን “ሉዓላዊነትና ዴሞክራሲ በኢትዮጵያ” በሚለው መጽሐፉ ጠቅሶ ቢያልፈውም፤ የደርግ ነፍሠ-በላዎች በፍርድ ቤት ቀርበው ተፈርዶባቸው፣ ታሥረው ግማሾቹም ከእሥር ተለቀው ታሪክ የሚሉትን የክለሳ ታሪክ በሚለቀልቁባት ሀገር፤ ስለ ኢሕአፓ የፖለቲካ እሥረኞች ጉዳይ የሚያነሳ አለመኖሩ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ሊያፍርበት የሚገባ ነው ባዮች ነን። ለምን ቢባል የኅሊና እሥረኞች ጉዳይ የሰብአዊ መብት ጉዳይ ስለሆነና እያንዳንዱንም ኢትዮጵያዊ ስለሚመለከት ሁሉም ሊጮኹላቸው በተገባ ነበር።

# አሲምባ ርዕሰ አንቀጽ

Editor’s Note ቁጥር 2/2010

የዚህ ርዕሰ-አንቀጽ መልዕክት በቅርቡ “የኢትዮጵያ ባለድርሻዎች ጉባኤ የማህበረሰባዊ ድርጅቶች ትብብር” በሚል ስም ከአራት ወራት በፊት በዳላስ ከተማ ሰሜን አሜሪካ የተቋቋመ (የድርጅቱን መሥራቾችና የተቋቋመበትን ምክንያት ለማንበብ ከዚህ ላይ ከድረ-ገጻቸው ላይ ያንብቡ http://www.tibibir.org/images/PDF/ECSO-Consortium-MOU-3.pdf ) እና ሌሎችም መሰል ስብስቦች በየቦታው የሚያደርጉት የተቀደሰ ተግባር እንዳለ ሆኖ፤ ወያኔ ወደ አዲስ አበባ ወደ ሥልጣን ሊመጣ ካለበት ጊዜ ጀምሮ ላለፉት 27 ዓመታት የተቋቋሙ ሕብረቶች፣ቅንጅቶችና ትብብሮች፣ ብዙም መግፋት ያልቻሉበት ምክንያት ለምንድር ነው? ብለው ቢጠይቁና ዕውነተኛ መልስ ቢያገኙ የተሳካ ትብብርን ማምጣት ይችላሉ የሚለውን ሃሳብ ለማካፈል ነው። ለነገሩማ በአንድ ድርጅት ጥላ ሥር ተሰባስበንም ወያኔን መጣል በቻልን ነበር።

የሕዝቡ ትግል አየል ብሎ ሲመጣ ወያኔን ውጥረት ውስጥ የሚያስገባውን ያክል በተቻለው መጠን ያለውን ኃይልና ዘዴ ሁሉ በመጠቀም የሕዝቡን ትግል ያመክናል ብሎም ብትንትኑን ያወጣዋል። ከሚጠቀምባቸው ዘዴዎች አንዱ በተቃዋሚው መካከል መተማመን እንዲጠፋ መካካድን ማስፋፋት፣ ሁነኛ መሪ ድርጅት ጠንክሮ እንዳይወጣ የተቻለውን ሁሉ ማድረግ። ለዚህም ተንኮሎ የሚደግፉት ኃያላን መንግሥታትንም ዕርዳት ያገኛል። ከተቃዋሚውም መካከል የኛኑ ጠማሞች በመካከላችን ውዥንብር እንዲያስነሱ ምልክት መስጠትና የመሳሰሉት ይገኙበታል።

በተቃዋሚው በኩል ደግሞ “ሥርገኛ መጣ በርበሬ ቀንጥሱ” እንዲሉ፤ የሕዝቡ ትግል አየል ሲል የሱቅ በደረቴ የፖለቲካ ድርጅቶችንና አስመሳዮችን ከየጉድጓዱ ብቅ አድርገን በተበታተነ መንገድ ለትግሉ ዝግጁ ነኝ ብሎ ዘራፍ ማለት! ለምሳሌም በሰሜን ኢትዮጵያ በጎንደር ሕዝብ መነሳሳትና አመጻ ወገናችን በደሙ እየከፈለ እኛ ደግሞ በደመ ነፍስ በስደት በርካታ የአማራ ድርጅቶችን ፈልፍለን መጠላለፍ (ሁሉም የአማራ ድርጅቶች ለአማራው መብት እንታገላለን እያሉን ማለት ነው)። ሕብረ-ብሔራዊ የፖለቲካ ድርጅቶችም መካከል እንደ አሜባ እየተቆራረጥን አንዳችን ከሌላው ያልተለየ የፖለቲካ ፕሮግራም እያራገብን ዴሞክራሲያዊ የፖለቲካ ድርጅት በሚል ስም የፈረደበት ድርጅት መፈልፈል። ይህ በሽታችን ደግሞ የማህበረሰባዊ ድርጅቶች እያልን የምንፈላሰፍባቸውንም ስለሚጨምር ህመማችን ተበራክቶአል። ሁሉም ትናንሽ ዙፋኑን ከኪሱ ይዞ ይዞራል ይባል የለ! ወያኔን ማቸነፍ የሚቻለው በተደራጀ ኃይል ነው ቢባልም ሺህ አንካሳ ድርጅቶችን በመፈልፈል በተናጠል እንደ እሳት እራት ቡን እንዲያደርገን ተመቻችተን ከቶውንም ሊሆን አይችልም። ወያኔ በምዕራባውያን ድጋፍ በኃይል ወደ አዲስ አባባ ከገሰገሰበትና የመንግሥት ሥልጣን በእጁ ከአስገባ አንስቶ ትንሽ ሊያስፈሩት የቻሉ ሁለት ወይም ሦሥት ሕብረቶች ተከስተው ነበር። ነገር ግን ተቃዋሚ ነን በሚለው ጎራ ውስጥ የተሰለፉ የሕብረቱ አባላት ከተስማሙበት የአጭር ጊዜና የሩቅ ጊዜ ስታራቴጂያዊ መርህና የመጫወቻ ሕግጋት አፈንግጠው የፖለቲካ ጥቅም ያገኙ መስሏቸው ከወያኔ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሚቁለጨለጭላቸውን ለመንከስ የቆሙበትን ከድተው እነሱም ጠፍተው በተቃዋሚው ጎራ መፈረካከስን አምጥተው አልፈዋል። ለምሳሌ በቅርቡ አቶ ሌንጮና ግንቦት ሰባት ሕብረት ወስጥ የተከሰተውን ያስተውሏል። ሌሎችንም እንደ እንቧይ ክበን የምንበትናቸውን ሕብረቶች መጥቀስ ይቻላል። ተስፋ ማስቆረጥ አይሁንብንና ዛሬ እኮ በውጪ ቢያንስ ሁለት ሕብረቶች አለን ይሉናል። አንደኛው ሸንጎ የሚባለው ሲሆን፣ ሌላው ደግሞ ከግንቦት ሰባት ጋር ተደረጉ የሚባሉ

የየምሽቱ ትብብሮች ናቸው። እነዚህ ስብስቦች ውጤት አልሰጥ ያሉት ለምን ይሆን ብለን ጠይቀናል? መጠየቅስ የሚያቅተን ለምንድር ነው?

ለማጠቃለል፦

ደጋግመን እንደምናስታውሰው የወያኔን ሥርዓት ለማስወገድ ኢትዮጵያውያን ከመቼውም ጊዜ የበለጠ ትግላችንን በኢትዮጵያዊነት ጥላ ሥር ብቻ በማቀነባበር ሁላችንም ወደ አንድ አቅጣጫ የምንገፋ የማንበገር ኃይል ሆነን መውጣት ይጠበቅብናል። ወያኔዎች ደግሞ ይህ ኢትዮጵያዊ ኃይል ተቀነባብሮ እንደ አንድ ሰው እንዳይወጣ የተቻላቸውን ማድረጋቸው አይቀሬ ነው። ስለሆነም "የኢትዮጵያ ባለድርሻዎች ጉባኤ የማህበረሰባዊ ድርጅቶች ትብብር" ዓይነት የሕብረት ጥሪ ሲመጣ የሚያበረታታ ዜና አድርገን የድጋፍ መግለጫ እንድናወጣ የሚጠብቁን ካሉ የዋሆች ብቻ ናቸው። እባብ የነደፈው ልጥ ሲያይ ይዘላል ነውና ይህንን ስብስብ በዳላስ መሠረቱ የሚባሉትን የማህበረሰባዊ ድርጅቶችና ወኪሎቻቸውን ስም ላነበብን ካብዛኛዎቹ የቆሸሸ የትግል ክህደት ታሪክና ማንነት ስንነሳ በፖለቲካ ድርጅቶች መካከል ትብብርን ሊያመጡ ይችላሉ ወይ? ብለን መጠየቃችን አይቀሬ ነው። አልበርት አይንስታይን እብደትን ሲገልጽ እንዲህ ብሎ ነበር ይላሉ። "Insanity is doing the same thing over and over again and expecting different results." ሲተረጎም "እብደት አንድን ነገር በአንድ ዓይነት መንገድ ብቻ መላልሶ በመሥራት የተሻለ ውጤት ማምጣት ይቻላል" ብሎ የሚያምን አብዷል ነው የሚለን።

በኢትዮጵያዊነት በሚያምኑ ድርጅቶች መካከል መተባበርና ጠንካራ ሕብረት እንደሚያስፈልግ አንጠራጠርም። ነገር ግን ሁላችንም ቆም ብለን መጠየቅ ያሉብን ነገሮች አሉ። እነሱም ሕብረት ከማን ጋር? ሕብረት ለምን? ሕብረት እንዴት? በ27 ዓመታት የሕዝብ ትግል ውስጥ አላዋቂ አዋቂዎች የተልፈሰፈሰ የእጅ መስጠት መፍትሄ ይዘው ብቅ እያሉ በመካከላችን ውዥንብር፣ ብተናና አሻጥር በመንዛት ለትግሉ መፋዘዝ ምክንያት መሆናቸውን እያወቅን ዛሬም ከተሞኘን ዕብዶቹ እኛ እንጂ ደላሎቹ አይደሉም።

ኢትዮጵያዊነት ያለጥርጥር በትግላችን ያቸንፋል።

የአሲምባ ድረ-ገጽ ዝግጅት ክፍል

ማሳሰቢያ፦

የአሲምባ ድረ-ገጽ ከማንኛውም ፖለቲካ ድርጅት ነፃ የሆነ ተቋም ነው። በእርግጥ ከቆምንለት ዓላማና፤ ታሪካዊ የትግል ታሪክ አንፃር ድረ-ገጻችን ለኢሕአፓ ከፍተኛ ከበሬታና ድጋፍ ቢሰጥም በድርጅቱ መዋቅር (የዕዝ ሠንሠለት) ውስጥ የተያዝን እንዳልሆነ እናስታውቃለን። ይህን ዓይነት ማሳሰቢያ የምንሰጥበት ምክንያት ባለፉት 12 ዓመታት ውስጥ ከዚህ መድረክ የሚሰነዘሩ ዕውነታዎች ተሰሚነት እንዳይኖራቸውም ሆነ ድረ-ገጹ ተጠያቂነትን በሕብረ-ሰባችን እንዲመጣ የሚያደርገውን ጥረት ከኢሕአፓ ጋር ያያይዙብናል

ብለን እንድንፈራ የሚያደረጉ ውሸቶች የሚያሰራጩ እንዳሉ ስለምናውቅ ነው። ስለሆነም ይህን ርዕሰ አንቀጽ አስመልክቶ የሚሰጡ አስተያየቶችን ለድረ-ገጻችን ዝግጅት ክፍል እንድትልኩልን እናሳስባለን።